# የቅጥፈት አጀንዳን በመቀባበል ዕውነታን መካድ ይቻላልን?

ዘአማን በላይ

bzaman@yahoo.com

የአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች ሰሞነኛ አጀንዳ ከሀገራችን አንፃር በአሳፋሪ ሁኔታ ተቀጣጥሏል። የኒዮ-ሊበራሉ ሚዲያ ሳር ቅጠሉ የሚመሰክረውን ሃቅ በሌለ ነባራዊ ሁኔታ አኮስምኖ ከማቅረብ ባሻገር፣ ፅንፈኞችን በመደገፍ የአንድ ወገን ዲስኩርን ለማስተላለፍ ሞክሯል። እርግጥ የምዕራቡ ሚዲያ የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች የፖለቲካ ሴራ ማራመጃ የሆነው ዛሬ አይደለም—ትናንትም ተመሳሳይ አጀንዳን ሲያራግብ እንደነበር የሚዘነጋ ዕውነታ አይደለምና። የአሁኑ ግን ትንሽ የሚያስገርም ነው። ሚዲያዎቹ ምናልባትም ካቋቋማቸው ሀገሮች አቋም አሊያም ርዕዮተ-ዓለም ውጪ አክራሪነትን ከፍ ብሎም ሽብርተኝነትን ከመዋጋትና አስከፊነቱን ከማጋለጥ ይልቅ፣ ጉዳዩን በመደገፍና በማንቆለጳጰስ ላይ መሰማራታቸው አንድም አስገራሚ፣ ሁለትም አሳፋሪ ነው። ነገሩ እንዲህ ነው።…

ሰሞኑን የአዲስ አበባ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ መስቀል አደባባይ በመገኘት የአክራሪነትን ድርጊት በመረረ ሁኔታ ማውገዝ ሰላማዊ ሰልፍ አድርጎ በዚያው መንፈስ ። መቼም በአደባባዩ የተገኘውን ህዝብ ቁጥር እንኳንስ እንደ እኔ ዓይነቱ ቦታ አጥቶ ከአደባባዩ ውጪ ሆኖ ስነ-ስርዓቱን የተከታተለ ሰው ቀርቶ፣ ተቃውሞውን በቴሌቪዥን የተከታተለም እንኳን ቢሆን ቁጥሩን ከአስር ሺዎች በላይ ሊሆን እንደሚችል መገመቱ አይቀርም። ቢቢሲ የተሰኘው የኒዮ-ሊበራል ሚዲያ ግን የሀገራችንን ሰላምና መረጋጋት በማይሹ ፅንፈኛ ኃይሎች በል ባሉት መሰረት “ትክክለኛነት” (accuraccy) የተሰኘውን የሙያውን ስነ-ምግባር አሽቀንጥሮ በመጣል ያለ አንዳች ሃፍረት “መስቀል አደባባይ መንግስትን ደግፎ ፅንፈኞችን በማውገዝ ለተቃውሞ የተገኘው ህዝብ ብዛት 1500 የሚጠጋ ነው። እንዲሁም የሰማያዊ ፓርቲ አባላት ታስረዋል፣ተደብድበዋል” ብሏል። ያው የተለመዱትንና አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች በአንድ ወቅት ለቀለም አብዮት ስራችን ያገለግሉናል ያሏቸውን፣ ከሀገራቸው ህዝብ ፍትሐዊና ሚዛናዊ ድምፅ ይልቅ በፈረንጆች “ዙፋን አንጋሽነት” የስልጣን እርካብን መቆናጠጥ የሚሹ “ሆድ-አደር” ተቃዋሚዎችን በመጥቀስ።

እንግዲህ በውጭ የሚገኘው የፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች አንዱ አርበኛ ሚዲያ ነው—ይህን አሳፋሪ አባባል በዘገባ መልክ ያቀረበው—አንድን ዕውነታ መዘገብ ማለት እንደሆነ ባላውቅም። ታዲያ አጀንዳው ከቢቢሲ ይገኝ እንጂ ጉዳዩን በመቀባበል ሁሉም ሊባሉ የሚችሉ የሀገራችን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የፈጠራቸው የግል መገናኛ ብዙሃን ‘እንደ ወረደ’ ቃል በቃል ገልብጠው በመለጠፍ ተቀባብለውታል—ጉዳዩ ትክክል ይሁን አይሁን ሳያጣሩ፣ የቢቢሲ ዘገባ አነሳሽ ምክንያት (motive) ምን እንደሆነ ሳያውቁ ብሎም ዘገባው ለተገነቡበት ስርዓት ምን ማለት እንደሆነ በቅጡ ሳያገናዝቡ። ታዲያ እኔም የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ ይህን አስገራሚ የውሸት ክምር ስመለከት፤ ‘የቅጥፈት አጀንዳን በመቀባበል ዕውነታን መካድ ይቻላልን?’ የሚል ጥያቄን አነሳሁ። እናም የትናንትና የዛሬን ተጨባጭ ሃቆች ተመርኩዤ የስም ማጥፋት “ክምሩን” እንዲህ በመናድ ለውድ አንባቢዎቼ ላስነብባችሁ ወደድኩ።…

…እርግጥ ቢቢሲ የተሰኘው የኒዮ-ሊበራል ጣቢያ በሰብዓዊ መብት ሽፋን የርዕዮተ-ዓለም ትግል የሚያካሂዱ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎችን አለባልታ እየቃረመ ብሎም እነርሱን ተክቶ እስከመስራት የደረሰ ተቋም ነው። እናም ለውሸቱ ማጠናከሪያ ይሆነው ዘንድ ለአቅመ-ተቃዋሚነት ያልደረሱ “አትርሱኝ” ባይ ፖለቲከኞችን ልቦለዳዊ ወሬ እንደ ትክክለኛ መረጃ በመውሰድ እንዲህ ዓይነቱን ከእውነት የራቀ ተግባር መከወን ለእርሱ አዲስ ነገር አይደለም። ትናንትም እንዲሁ ነበር—የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎችን ትዕዛዝ እየተቀበለ በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ላይ በርካታ መሰረተ-ቢስ ውንጀላዎችን በመደርደር የስም ማጥፋት አሳፋሪ ተግባሩን ሲያካሂድ የቆየ መሆኑን። እስቲ ለማንኛውም ሌሎቹን ትተን የቅርብ ጊዜ ሁለት አፈ-ታሪኮቹን እነሆ ልበላችሁ— ከሚዲያ ተግባሩ ወጥቶ ሂዮማን ራይትስ ዎችን በመተካት ኢትዮጵያ ውስጥ የእርዳታ እህል ለፖለቲካ ጥቅም እንደሚውል አስመስሎ ያቀረበውን እንዲሁም ከ25 ዓመት በፊት ህወሓት የዕርዳታን ገንዘብ ለመሳሪያ ግዥ አውሎታል በማለት የሰራውን ኮሜዲ ድራማ በማስታወስ።

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ ቢቢሲ “ጋዜጠኞቹን ወደ ኢትዮጵያ በቱሪስት መልክ በመላክ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ዘዴ ተጠቅሜ ያገኘሁት መረጃ ነው” በማለት የእርዳታ እህል ለፖለቲካ ጥቅም እየዋለ ነው ሲል የተለመደ ቅጥፈቱን የቀጠለው የየትኛውንም ተቋም መግለጫ ሳይጠብቅ በራሱ ተነሳሽነት ነበር፡፡ ታዲያ በወቅቱ ‘ቢቢሲ የማንን ተግባር  እየተወጣ ነው?’ የሚል ጥያቄ በበርካታ

ሀገር ወዳድ ዜጎች መነሳቱ የሚታወስ ነው። ግና ምላሹ ቀላል ነበር።...አዎ! ቢቢሲ በእንግሊዝ ህዝብ ታክስ የሚተዳደርና በዋነኛነትም አገልግሎት የሚሰጠው ለዚሁ ዜጋ ነው። ይሁንና የዕርዳታ እህል አሰጣጥን በተመለከተ በየዓመቱ የቤተክርስቲያን ስዕለት ያለበት ይመስል በሀገራችን ላይ የሚነዛው አሉባልታ፤ ተግባሩን እየተወጣ ያለው ለሌላ "ኃይል" መሆኑን ለመገንዘብ አልከበደም። እርግጥም ያካሄደው የስም ማጥፋት ዘመቻ ሌሎቹ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ያልተሳካላቸውን አጀንዳ ነው። ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው፤ እነ ሂዮማን ራይትስ ዎችን የመሳሰሉ ፅንፈኛ ኒዮ-ሃይሎች በተደጋጋሚ የህዝቡን ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነት በመጋፋት የራሳቸውን ተላላኪዎች (በተለይም እሳትና ጭድ የሆኑትን የመድረክ አመራሮችን) "ዙፋን ለማስነገስ" በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ሳያሰልሱ ያደረጉት ጥረት በዴሞክራሲያዊ ምርጫ በሚያምነው ሚዛናዊው የኢትዮጵያ ህዝብ አማካኝነት ከሽፏል፡፡ በዚህም ፅንፈኛ ኒዮ- ሊበራሎቹን "ከሉዓላዊ ስልጣኔ ላይ እጃችሁን አንሱ!" የሚል ግልፅና የማያወላዳ ምላሽ ሰጥቷቸዋል፡፡

እነርሱ ግን አርፈው አልተቀመጡም፡፡ የ"አንጋሽነት" ምኞታቸው ሲጨነግፍባቸው በሦስት ወር ልዩነት "በሰብዓዊ መብት" ሽፋን በሀገራችን ላይ የውሸት መግለጫ ጋጋታ ያዥጎደጉዱ ጀመር፡፡ ዋነኛ ዓላማቸውም ከሊበራሊዝም ርዕዮተ- ዓለም ውጪ በራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ፈጣንና ተከታታይ በሆነ መልኩ የሚያድጉ ሀገራትን ማጣጣልና የህዝብ ድጋፍ የሌላቸው አስመስሎ ማቅረብ ነው። እናም እንደ ቢቢሲ ዓይነቱን የኒዮ- ሊበራሊዝም አቀንቃኝ ሚዲያዎችን በግንባር ቀደምትነት መጠቀም ምርጫቸው ነው፡፡ ለዚህም እንደ አብነት ከምርጫ 2002 በፊትና በኋላ "ጫና መፍጠሪያ አንድ መቶ መንገዶች"፣ "ለፖለቲካ መሣሪያ የሚውለው እርዳታ"...ወዘተርፈ የሚሉ የሂዮማን ራይትስ ዎችን የፈጠራ ሪፖርቶች ያለ አንዳች ማረጋገጫ ቢቢሲ ቀዳሚውን ስፍራ ወስዶ ሲያንበለብለው እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

ነገር ግን በወቅቱ ሂዩማን ራይትስዎች የተባለው ፅንፈኛ ኒዩ-ሊበራል ተቋም "የኢትዮጵያ መንግስት ዕርዳታን ለፖለቲካ መሳሪያነት እየተጠቀመበት ነው" በማለት ያወጣው የተለመደ የቅጥፈት መግለጫን፤ ሀገራችን ውስጥ በስራው ላይ የተሰማሩትና በምህጻረ ቃል "ዳግ" (DAG) እየተባሉ የሚጠሩት ከ26 በላይ የሚሆኑ የልማት አጋር ቡድን አባላት ባደረጉት ጥልቅ የማጣራት ስራ፤ የእርዳታ እህል ለፖለቲካ ጥቅም መዋሉን

ማረጋገጥ አልቻልንም” በማለት የፅንፈኛውን “ድርጅት” ውሸታምነት የዓለም ህዝብ እንዲያውቀው በአደባባይ ተናግረዋል፡፡

ታዲያ የእንግሊዝ መንግስት አባል በሆነበት የልማት አጋሮቻችን ቡድን ጭምር በሚገኙበት “ዳግ” አማካኝነት የፈጠራ ሪፖርቱ የተጋለጠው አክራሪው ኒዩ - ሊበራል ተቋም ከእንግዲህ ውሸቱ ይፋ መወጣቱንና ቢለፈልፍም የሚሰማው እንደማይኖር ስለተገነዘበ ሃፍረት ለምኔ የሆነውን ቢቢሲን ተጠቅሞበታል፡፡ እርግጥ ከኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮተ-ዓለማዊ ትስስር አኳያ የሁለቱ ተቋሞች ጥምረት “አፍንጫ ሲመታ፣ ዓይን ያለቅሳል” እንዲሉት ዓይነት በመሆኑ፤ ከእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ጋር ተነጋግሮ “ቱሪስት በመምሰል ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቼ አገኘሁት” ያለውንና እነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ከዛሬ ሶስት ዓመት በፊት ሞክረውት ያልተሳካላቸውን የማጥላላት ዘመቻ ያለ ይሉኝታ ደግሞታል። ይህም ጣቢያው ከጋዜጠኝነት ተግባሩ ወጥቶ ሂዩማን ራይትስ ዎችን ተክቶ እየሰራና አጀንዳውንም በዘገባ መልክ እያራመደለት መሆኑን አፍ አውጥቶ የሚናገር ዕውነታ ነው፡፡ …ታዲያ ውድ አንባቢዎቼ ሰሞኑን መስቀል አደባባይ ወጥቶ አደባባዩን ከአፍ እስከ ገደፉ የሞላውንና ቁጥሩ እጅግ ከፍተኛ የሆነውን ህዝብ ጣቢያው ለምን እጅግ በጣም አሳንሶ ወደ 1500 እንዳወረደው እዚህ ላይ ልብ ይሏል!...

አሁን ደግሞ እስቲ ወደ ሁለተኛው ጉዳይ እንዝለቅ—ከ25 ዓመት በፊት ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ የዕርዳታን ገንዘብ ለመሳሪያ ሸያጭ አውሎታል ስላለው ድራማዊ ትወናው። ነገሩ እንዲህ ነበር።…የዛሬ ሶስት ዓመት ገደማ ጣቢያው በ1977 ዓ.ም በተከሰተው ረሃብ በወቅቱ የህዝቦችን የዘመናት መሰረታዊ ጥያቄዎችን አንግቦ መታገል ላይ የነበረውን ህዝባዊ ኃይል (ህወሓት) “የዕርዳታ እህልን ለጦር መሣሪያ ግዥ አውሎታል” የሚል የፈጠራ ዘገባ አቅርቦ፤ ብዙም ሳይቆይ የዕርዳታው አስተባባሪ የነበሩትን ታዋቂው ስር ቦብ ጊልዶፍን “ተሳስቻለሁ” በማለት ይቅርታ ጠይቋል፡፡ ይሁንና ሆን ብሎ የጉዳዩ ባለቤት የሆነውን የኢትዮጵያን መንግስትና ህዝብ ምንም ዓይነት ይቅርታ ለመጠየቅ አልፈለገም። ምክንያ ደግሞ ግልፅ ነበር። እርሱም ጣቢያው ለእነ ሂዩማነ ራይትስ ዎች ያለውን ታማኝነት ለመግለፅ የተጠቀመበት የወገንተኝነት ዘዴ ስለሆነ ነው፡፡ ታዲያ ይህ ሌላኛው ተግባሩ “ዕውን ቢቢሲ ሚዲያ ነው ወይስ ‘ለትርፍ ያልተቋቋመ’ ሲቪክ ማህበር?” የሚል ጥያቄ ሀገር ወዳድ በሆኑ ዜጎች ውስጥ መፈጠሩ የሚዘነጋ አይደለም። እርግጥም ጣቢያው በእንግሊዝ ህዝብ ግብር እየተዳደረ፣ በተግባር ግን “ኃላፊነቱ የተወሰነ የእነ ሂዩማን

ራይትስ ዎች የግል ማህበር" ላለመሆኑ ማንም በእርግጠኝነት ሊናገር የሚችል አይመስለኝም።

ያም ሆነ ይህ ግን ውድ አንባቢዎቼ ቀደም ሲል ካቀረብኳቸው ሁለት ምሳሌያዊ የጣቢያው ተግባሮች፣ ቢቢሲ ከኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት አኳያ የሚከተለውን በቅጥፈት ላይ የተመሰረተ መረጃም ይሁን ማስረጃ አልቦ የዘገባ አቅጣጫን እንዲሁም በራሳቸው ፖለቲካዊ እሳቤ በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገራት ላይ በቅጥፈት የሚተኩሰውን የአሉባልታ ጥይት እንደተገነዘባችሁ ተስፋ አደርጋለሁ—ሰሞነኛው "መስቀል አደባባይ መንግስትን ደግፎ ፅንፈኞችን በማውገዝ ለተቃውሞ የተገኘው ህዝብ ብዛት 1500 የሚጠጋ ነው። እንዲሁም የሰማያዊ ፓርቲ አባላት ታስረዋል፣ ተደብድበዋል" በማለት ሃቁን አወላግዶ ያቀረበው አፈ-ታሪኩም የእነዚህ ተግባሮቹ ቀጣይ ክፍል መሆኑንም ጭምር።

እንደሚታወቀው በርካታ ወገኖች 'ሰማያዊ ፓርቲ አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች ሀገሪቱ ውስጥ በቀለም አብዮት አማካኝነት ሁከት መቀስቀሻ ይሆን ዘንድ ያዘጋጁት ሊሆን ይችላል' የሚል እምነት አላቸው። እኔም የእነዚህን ወገኖች እምነት እጋራለሁ። ለምን ከተባለ ፓርቲው ገና የፖለቲካን 'ሀሁ' የማያውቅ ጮርቃ ቢሆንም፣ በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሰላም ይልቅ ነውጥን የሚያልም የአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች 'ቅምጥ' መሆኑን ነገረ-ስራው ሁሉ አፍ አውጥቶ ስለሚናገር ነው— "የምትናገረውን እንዳልሰማህ ምግባርህ ይጮህብኛል" እንዲሉ ታታሪዎቹ ጃፓኖች።

እርግጥም ፓርቲው ህገ-መንግስቱን አክብሮ ሃሳቡን በሰላማዊ መንገድ ለማራመድ ከምርጫ ቦርድ የዕውቅና የምስክር ወረቀት ቢያገኝም ቅሉ፣ በማግስቱ ከጥቂት ሃይማኖታዊ አክራሪ ፖለቲከኞች ጋር ተዳብሎ በሰላማዊ ሰልፍ ስም ያከናወናቸውን አመፅ ናፋቂ ተግባራቱ፣ ከእርሱ በፊት የተቋቋሙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ከተጣመራቸው በኋላ በፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ኢ-ኢትዮጵያዊ ግብረ ገብነት ከአቅሙ በላይ በመመፃደቅ 'አትረቡም' በሚል ቃና ተሳድቦ መውጣቱ (ምንም እንኳን ፓርቲዎቹ 'ምን ለምን አብረህ አዝግም' እንዲሉት ዓይነት ቢሆኑም) እንዲሁም ሰሞኑን ጥቂት አባላቱ አክራሪነትን በማውገዝ በነቂስ የወጣውን የአዲስ አበባ ህዝብን የሰላም ዝማሬን ለማወክ ያደረጉት ሙከራ የዚህ ማንነቱ ህያው አስረጅ ናቸው ብዬ አምናለሁ። በተለይም ፓርቲው 'እንበጠብጠዋለን' በሚል ፀረ-ሰላም እሳቤው ያለ ከተማው መስተዳድር ፈቃድ "አሳውቄያለሁ" በሚል ደረቅ ሙግት ህዝቡ የሚያደርገውን ሰለማዊ ሰልፍ የማወክ

ሙከራው፣ ቀደም ሲል ከገለፅኩትና አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች የኢትዮጵያን መንግስትና ህዝብ ሰናይና ገንቢ ተግባራትን የማጣጣል ብሎም በቅጥፈት መንግስት ህዝባዊ ድጋፍ የሌለው የማስመሰል ሴራዊ አካሄድ ጋር ምንም ዓይነት ልዩነት የሌለው በመሆኑ፣ ይህን እምነቴን እንዳጠናክር የሚያደርገኝ ነው። ምክንያቱም እኛ እዚህ ሀገር ተቀምጠን ሁሉንም ነገር በዓይናችን ከምናየውና በጆሮአችን ከምንሰማው ተጨባጭ ዕውነታ ወዲያ ሌላ እማኝ ፈልጎ ማግኘት አይቻልምና።

ያም ሆነ ይህ ግን እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ሰማያዊ ፓርቲ ከላይ እንደጠቀስኩት ባህሪያዊ ማንነቱ በሀገር ውስጥ ጉዳይ ፈፃሚነት አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎችን ለማስደሰት ሲል ቀዳሚ ስራው ሁከት መናፈቅ በመሆኑ፣ ወትሮም ጥቂት የሆኑት አባላቱ (የወሃቢን ፅንፈኛ ፖለቲከኞች ጨምሮ ማለቴ ነው) የአዲስ አበባን ህዝብ የሰላም ፍላጎት ለመበጥበጥ ሲያሴሩ ከተገኙ በፖሊስ በህጉ መሰረት ህጋዊ የእርምት እርምጃ ከወሰደ እሰየው የሚያስብል ነው። ምክንያቱም ፖሊስ የህዝቡን ዕለታዊ ደህንነት ከመጠበቅ ባሻገር፣ የፖለቲካ ሰልፎች ሲካሄዱ በቂ ጥበቃ በማድረግ የህዝቡን ሰላማዊ ህይወት ከአደጋ የመከላከል ኃላፊነትና ግዴታ ስላለበት ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ዋነኛ ዓላማው ህገ-መንግስቱን ከውስጥና ከውጭ ፀረ-ሰላም ኃይሎችና አሸባሪዎች መከላከል ስለሆነ ይህን ህዝባዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት በሀገሪቱ አስተማማኝ ሰላም የማስፈን ተልዕኮውን በአግባቡ ለመወጣት ህገ-ወጦችን አደብ ማስገዛት ይኖርበታል። እናም ምናልባት ፖሊስ የሰማያዊ ፓርቲ እፍኝ የማይሞሉ አባላትን ለህገ-ወጥ የሴራ ዱለታ ሲዘጋጁ ደርሶባቸው አደጋው ከመድረሱ በፊት በቁጥጥር ስር አውሏቸው ከሆነ ያከናወነው ተግባር ህግና ስርዓትን የማስጠበቅ መደበኛ ስራው ስለሆነ አዲስ ነገር የለውም ባይ ነኝ።

ይሁንና የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎችን ተልዕኮ ሀገር ውስጥ ለማስፈፀም የሚቧችረው ሰማያዊ ፓርቲ “ፖሊስ አባሎቼን ደብድቧል” የሚለው ስሞታው ያው የተለመደው የእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ክስ በመሆኑ ውሃ የሚቋጥር አይደለም። ይህኛው የስም ማጥፋት ዘመቻም እነርሱን ለማስደሰት ሲባል የቀረበ ነው። ምክንያቱም እነ ሂዩማን ራይትስ ዎች በተለያዩ ጊዜያት በዲሲፕሊኑ የሚታወቀውን የሀገራችንን ፌዴራል ፖሊስ ያለ ስሙ ስም በመስጠት የሪፖርት ጋጋታ ሲያወጡ እንደነበር የሚታወቅ ነው። እናም ፓርቲው ይህንኑ ያልተሳካ ሙከራ መድገሙ ሀገር ውስጥ የተቋቋመበት መደበኛ ስራው ስለሆነ ምንም የሚደንቅ ነገር የለውም። እያከናወነ ያለው ነገር የተመደበበትን ‘ስራ’ ነውና።

ያም ሆነ ይህ ግን ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ በአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች የርዕዮተ-ዓለም ትግል አማካኝነት በሀገራችን ላይ እየተካሄደ ያለውን የቅጥፈት አጀንዳ ቅብብሎሽን እንዲገነዘብልኝ እሻለሁ። የቅብብሎሹ የስበት ማዕከል ታዳጊ ሀገሮች በራሳቸው የልማት መስመር ተጉዘው ለውጥ ሲያመጡ ዓይናቸው ደም የሚለብሰው ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራሎች መሆናቸውንም ጭምር። እርግጥም የውሸት አጀንዳው ፈጣን ቅብብል በእነዚህ ሃይሎች ፊታውራሪነት የሚካሄደው እንዲህ ነው።…

…ገና ከጅምሩ እነ ቢቢሲም ይሁን እንደ ሰማያዊ ፓርቲና መድረክ  ዓይነት የሀገር ውስጥ ሆድ-አደር ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተቃዋሚነት ስም ሲደራጁ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች ከእነርሱ ጋር "ዞሮ-ገጠም" ክብ እንዲሰሩ ይፈልጋሉ። ጉዳዩን በአጭሩ ለመግለፅ ያህል፤ የሀገራችንን ዕድገት የማይሹት አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎቹ በየሀገሩ የሚቋቋሙ ወይም ራሳቸው የሚያቋቁሟቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በፋይናንስ ይደግፏቸዋል።በዚህ መንገድ ለተቋቋሙት ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በሀገራቱ ውስጥ ከነባራዊው ሁኔታ ውጪ የሆኑ ፍፁማዊ (absolute) የሰብዓዊ መብት፣ የፕሬስ ነፃነት፣ የዴሞክራሲ ጉዳዮች…ወዘተ. አለመከናወናቸውን የሚያትቱ አሉባልታዎችን እየነቀሱ ለየሚዲያው መግለጫ እንዲሰጡ ጥብቅ ትዕዛዝ ያስተላልፉላቸዋል። ፓርቲዎቹም "የበሬ ምንትስ ይወድቃል ብላ ስትከተል ዋለች" እነደተባለችው እንስሳ በውጭ ሀገር አንጋሽነት የሚገኝ ስልጣን ያለ ስለሚመስላቸው ይህንኑ ያደርጋሉ።…ቢቢሲን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ደግሞ ወሬውን ተቀብለው ያለ አንዳች ማስረጃና ሚዛናዊነት ጉዳዩን ያጦዙታል ወይም እንዲያጦዙት ይታዘዛሉ።

…እነ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ ሲ.ፒ.ጄና አምንስቲ ኢንተርናሽናልን የመሳሰሉ አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎችም፤ በየሀገሩ ከፈለፈሏቸው ተቃዋሚዎችና "ጉዳይ ፈፃሚ" የፕሬስ ውጤቶች ከሚደርሷቸው ስብቀቶች በተጨማሪ፤ የራሳቸውን ትዕዛዝ መልሰው በቢቢሲ ምንጭነት መዝግበውም ይይዟቸዋል። ከዚያም ከእነርሱ አመለካከት ውጪ በራሳቸው የልማት አማራጭ ማደግ በጀመሩ እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት ሀገራት ላይ በየሶስት ወሩ የመግለጫ ጋጋታ ያወጣሉ። በዚህም የመግለጫው የመጀመሪያና የመጨረሻ ተወናዮች አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎቹ ይሆናሉ። እርግጥም በክቡሩ ሰብዓዊ መብትና በጋዜጠኝነት መብት ተቆርቋሪ ስም የውሸት ስለላን የማካሄድ "አልፋና ኦሜጋ" ይኋል እንዲህ ነው፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ውድ አንባቢዎቼ ሰማያዊ ፓርቲ ሰሞኑን 'መንግስትን በመደገፍ አደባባይ የወጣው ህዝብ ብዛት 1500 ነው፣ አባሎቼ በፖሊስ ታሰሩ፣ ተደበደቡ ምንትስ' በማለት ያቀረበውን

የቅጥፈት ወሬ በመጀመሪያ ቢቢሲ መዘገቡን ስትመለከቱ፤ በፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች፣ በሰማያዊ ፓርቲና በቢቢሲ መካከል ያለውን የአጀንዳ ቅብብሎሽ በግልፅ እንደምትገነዘቡ እርግጠኛ ነኝ። የአሉባልታው የመጀመሪያና የመጨረሻ ምንጭ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራሎቹ መሆናቸውንም እንዲሁ።…ግና 'ሰማያዊ ፓርቲስ?' ብላችሁ እንዳትጠይቁኝ። "…እውነት…እውነት እላችኋለሁ፤ ሀገርን ከዶ የባዕድ ጉዳይ ፈፃሚ ከመሆን ይሰውራችሁ" ከማለት ሌላ የምሰጣችሁ አንዳችም ዓይነት መልስ የለኝምና።

ታዲያ ውድ አንባቢዎቼ ይህ የቅጥፈት ቅብብሎሽ አጀንዳ ወደ ሀገራችንም የግል ፕሬሶች እንዲዛመት መደረጉን መዘንጋት የለባችሁም። ምክንያቱም የሀገራችን የግል ሚዲያዎች እዚሁ ሀገር ውስጥ ቁጭ ብለው ለሰላማዊ ሰልፍ የወጣውን እጅግ ብዙ ህዝብ በዓይናቸው እየተመለከቱ እነ ቢቢሲን እንደ ትክክለኛ ምንጭ በመጥቀስ ያቀረቡትን የተሳሳተ ዘገባ መመልከታችሁ ስለማይቀር ነው። ግና ይህ አሳፋሪ ተግባራቸው መልሶ ራሳቸውን የሚያስገምት ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ መስቀል አደባባይ ሰላምን ሽቶ እንዲሁም አክራሪነትን አውግዞ የወጣውን ህዝብ የሰላም ቀናዒ ፍላጎትን ከማጉላት ይልቅ፤ ከእነ ወሃቢ አክራሪዎች ጋር ለሁከት ተሰልፎ የቆመውን ሰማያዊ ፓርቲን 'እንዲህ ሆነ' በማለት ጉዳዩን ለማጫጫህ ሞክረዋል—የቢቢሲን ዘገባ ቃል በቃል በመዋስ።

በእኔ እምነት በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው የሚዲያ ተግባራቸውን በሰላማዊ መንገድ እያከናወኑ ያሉት እነዚህ ፕሬሶች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች የሐሰት አጀንዳ ቅብብሎሽ ሰለባ ሆነዋል። ምንም እንኳን ሚዲያዎቹ ባያውቁትም አሊያም አውቀው ቢያደርጉትም፤ እዚህ ሀገር ውስጥ አስተማማኝ ሰላም ከሌለ እንኳንስ ስራን ለመከወን ቀርቶ በሰላም ገብቶ መውጣት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። እናም የግል ፕሬሶቹ የሁከትና የብጥብጥ መንገድን የሙጥኝ ብሎ የያዘን አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ ሁኔታ ከአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተልዕኮው አኳያ ለቢቢሲ ያለውን ነገር ያለ አንዳች ማጣራት እንዳለ በመውሰድ ለህዝብ ማሰራጨታቸው ተገቢም ትክክልም አይደለም።

በመጀመሪያ ደረጃ ለእኛ ሀገር የሚበጀን የዘገባ ዓይነት የህዝቡን ልማታዊ ተግባራት የሚደግፍ እንጂ፤ በየመስኩ ተሰማርቶ ዕድገትን በተሻለ ሁኔታ ነገ ለማየት የሚሻን ታታሪ ዜጋን የስራ መንፈስ የሚበርዝና ወደ ላላስፈላጊ አተካራ ውስጥ የሚያስገባ መሆን የለበትም። እናም የዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ምቹ ሁኔታ የፈጠራቸው የግል ሚዲያዎቹ "ወፍ

እንዳገሩ ይሮጣል" የሚለውን ሀገራዊ ይትብሃል ከስራቸው አኳያ መጠቀም ይኖርባቸዋል። እንደሚታወቀው ማንኛውም ሚዲያ የተገነባበት ማህበራዊ-ኢኮኖሚ አውድ (Context) ነፀብራቅ ነው። በመሆኑም በሀገራችን ውስጥ እየተገነባ ያለውን ስርዓት ቅጥ ባለው መንገድ መረዳት ተገቢ ይመስለኛል። በአሁኑ ወቅት እየተገነባ ያለው ስርዓት ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ እንጂ፤ ሊበራሊዝም አይደለም። ስለሆነም ሚዲያዎቹ ለህዝብ እናስባለን የሚሉ ከሆነ መሆን የሚገባቸው የስርዓቱ ነፀብራቅ እንደሆነ መገንዘብ ያለባቸው ይመስለኛል።

በሊብራሊዝም ስርዓት ውስጥ ልማታዊ አስተሳሰብ ያለው ፕሬስ እንደማይገነባ እንደማይችል ወይም ቢገነባም ጠብ የሚል ነገር እንደማያመጣ ሁሉ፤ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥም የሊበራሊዝም አቀንቃኝ የሆነ ሚዲያ ቢገነባ ምናልባትም ከአደናቃፊነት የዘለለ ሌላ ፋይዳ ላይኖረው እንደሚችል መረዳት ያባት ነው። ታዲያ ውድ አንባቢዎቼ ይህን ስል በሀገራችን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ የግል ሚዲያዎች አያስፈልጉም እያልኩ እንዳልሆነ እንደምትገነዘቡልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ይልቁንም እያልኩ ያለሁት የግሉ ፕሬስ የየትኛውም ሀገር ሚዲያ እንደሚያደርገው ዘገባውን ከሀገራዊ ጥቅም (National Interest) አኳያ በሚገባ እየቃኘ ከሰራ፤ በመካሄድ ላይ ላለው የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታ ስር መስደድ የበኩሉን ሚና ሊጫወት እንደሚችል ለመጠቆም ነው።

ያም ሆነ ይህ ግን በርዕሴ ላይ ያነሳሁትን 'የቅጥፈት አጀንዳን በመቀባበል ዕውነታን መካድ ይቻላልን?' የሚል ጥያቄን ስናነሳ ምላሹ "በፍፁም" የሚል ሆኖ እናገኘዋለን። እርግጥም የአክራሪ ኒዮ-ሊብራሎች የሐሰት አጀንዳ ቅብብሎች ሀገራችን ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ሊደፈጥጠው አይችልም። ለምን ከተባለ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ልማታዊ ዴሞክራሲያዊው ስርዓት በፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ እየተመሩ እጅግ አጣዳፊ በሆነ የልማት ስራ ውስጥ በመሆኑ ቅጥፈትን ሊሰማ ስለማይችል ነው። ጊዜ የለውም። ከሁሉም በላይ ደግሞ በሰላሙ ላይ የመጡበትን ኃይሎች የማዳመጥ ባህል የለውም—ትክክለኛነታቸው በተግባር በተረጋገጠው የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እየተመራ በራሱ ጥረት ባስገኘውና ተጠቃሽ ከሆነበት የዕድገት ማማው ላይ ባይሳካላቸውም ጎትተው ሊያወርዱት እንደሚሞሩ ጠንቅቆ ያውቃልና። ታዲያ ይህ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አክራሪው ኒዮ-ሊበራል ኃይል የሀገራችንን ህዝብና የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ

መንግስቷን ሰላማዊ ጥረት ለማኮስመን የሚያደርጋቸው ግልፅና ስውር የሐሰት ወሬ ቅብብሎሽ ዘመቻዎች የበረሃ ጩኸት ሆነው እንደሚቀሩ የሚያመላክት ነው። አማን እንሰንብት።